# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو


Gaafa: 01-08-2012 ibsa تاريخ

Lakk.: No.: 011/-abo/2012 رقم

## የኦሮሞ ህዝብ በማናቸውም ኣደናጋሪ ፕሮፓጋንዳዎች ሳይታለል የተያያዘውን ፍትሃዊ ትግል ማፋፋም የወቅቱ ጥያቄ ነው

### የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ

ባለፉት ሁለት ወራት “የኦሮሞ ውይይት መድረክ” ብሎ ራሱን የሰየመ ኣንድ ቡድን የኦሮሞ ህዝብ በድርጅቱ ኦነግ ላይ ያለው እምነትና ተስፋ ኣንዲደበዝዝ ለማድረግ በኣፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ተጠምዷል። ለኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል የተቀረቀረ እያስመሰለ ኦነግን ለመናድ የሚነዛውን የዚህን ስብስብ ኣፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ኦነግ በጥንቃቄና በትእግስት በመከታተል እውነትና ቅጥፈትን ለይቶ ለህዝቡ ሲያሳውቅ ቆይቷል። ኣሁን የሚስተዋለው ኣፍራሽ ፕሮፓጋንዳም የከዚህ ቀደሙ ቀጣይ ኣካል በመሆኑ የሚከተለውን ሃቅ ህዝቡን ማስገንዘብ የግድ ይለናል።

የተጠቀሰው ስብስብ የኦነግን ህግና ደንብ የተጻረረ ዘመቻውን ገፍቶበት ኣፍራሽ ፕሮፓጋንዳውን ወደ ኣለም ኣቀፍ መገናኛ ብዙሃን እያሳደገ እንደሚገኝ ግልጽ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ የኦሮሞ ትግል ውስጣዊ ጉዳይ ሲባል የቆየውን ኣርእስት በውጪው ሚድያ ላይ ማቅረቡና ይንንም ኣን ድ ብሎ ሲጀምር የኣሜሪካ ድምፅ ሬድዮ የኣማርኛውን ኣገልግሎት መምረጡ ለምን እንደሆ ነ በርካቶችን እያነጋገረ ነው። ከስብስቡ ኣመራር ኣባላት መካከል ኣንዱ ሃምሌ 28, 2012 ከ ቪኦኤ ኣማርኛው ኣገልግሎት ፕሮግራም ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ “የኦሮሞ ውይይት መድረክ” የተሰኘው ስብስብ ምን እንደሆነና ለምንስ ኣላማ እንደቆመ ከጉዳዩ ባለቤት ከኣፋን ኦሮሞው ኣድማጭ ህዝባችን ኣስቀድሞ የኣማርኛው ኣድማጭ ወገን እንዲገነዘብላቸው መረጡ። በውጪው ኣለም ለሚነዙት ኣንዳንድ ጸረ ኦነግ ፕሮፓጋንዳዎች እንግዳ የሆነው የሃገር ቤቱ ሰፊው ህዝባችን ለመጀመሪያ ጊዜ ስለዚህኛው ጉዳይ የሰማው የራሱን ውስጣዊ ጉዳዮች በሚያስ ተናግደው የኣፋን ኦሮሞ ቁዋንቁዋው ኣልነበረም። ይህም የሚያሳየው የስብስቡ ኣብይ ኣላማ ለኦሮሞ ህዝብ ችግር ተቆርቁሮ መፍትሄ ማፈላለግ ሳይሆን የኦሮሞን ህዝብ ትግል ውድቀት የሚመኙ ወገኖችን የምስራች ለማለት የተጣደፈ መሆኑን ኣረጋገጠ።

ይሁን እንጂ መሬት ላይ ያለው ሃቅ ግልፅ ነው። ከላይ በተጠቀሰው እለት በተደረገው ቃለ-መጠይቅ ላይ የቀረቡት እንግዳ እንደመሰከሩት “የኦሮሞ ውይይት መድረክ” በተሰኘው ስብስብ ውስጥ የታቀፉት ግለሰቦች ካሁን ቀደም በስነ ምግባር ጉድለትና በስርኣት ኣልበኝነት ሳቢያ ከኦነግ የተባረሩና በትግሉ ላይ የነበራቸው ሞራልና ቁርጠኝነት በመዳከሙ ከድርጅቱ የተንጠባጠቡ ወገኖች መሆናቸው ግልፅ ነው። “የኦሮሞ ውይይት መድረክ” የተሰኘው ቡድንም በተጠቀሱት ምክንያቶች ሳቢያ ከኦነግ ጋር መራመድ ያቃታቸውን ግለሰቦች ካሉበት እያፈላለገ የመለመላቸው ግለሰቦች ስብስብ ነው።

እዚህ ላይ ለህዝባችን ግልፅ መሆን ያለበት ኣንድ ኣብይ ነጥብ ኣለ። ስሙ የተጠቀሰው ይህ ቡድን ባሁኑ ጊዜ “ኦነግ ብዙ ቦታዎች ላይ ተከፋፍሏል” የሚለውን እያጋነነ ይለፍፋል። የኦነግ ኣመራር እጅግ ኣስቸጋሪና ውስብስብ በሆነ ሁኔታ ውስጥ መልከ-ብዙ ተግዳሮቶችን ተቋቋቁሞ በቁርጠኝነት የሚመራውንና እጅግ መራራ መስዋእትነቶችም እየተከፈሉበት ያለውን ትግል በሚያሳፍር ሁኔታ እያብጠለጠለ የኣመራሩን፣ የኣባላቱን፣ የደጋፊዎቹንና ባጠቃላይ ከትግሉ ጎን


P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea |Tel 2911 153848 | E-mail abamilki@gemel.com.er www.oromoliberationfront.org

ተሰልፎ የሚገኘውን ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ተስፋ ለማስቆረጥ ቡድኑ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። ኦነግ ከረጅም ጊዜ በፊት ጀምሮ በተፈጠረው የውስጥ ችግር ተተብትቦ መቆየቱ የሚካድ ኣይደለም። መዘንጋት የሌለበት ሃቅ ግን ከመጀመሪያው ኣንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ኦነግ ላይ ለደረሰውና ኣሁንም እየደረሰ ላለው ጉዳት በቀዳሚነት የሚጠየቁት እነዚሁ ዛሬ "የኦሮሞ ውይይት መድረክ" የሚል ስብስብ ሰይመው የሚመሩ ግለሰቦች መሆናቸውን ለጉዳዩ ቅርበት ያለው የድርጅታችን ኣባልና ህዝባችን በግልጽ ይረዳል። ለጉዳዩ እንግዳ ለሆኑት ወገኖች ደግሞ የምናስገነዝበው ነገር ቢኖር ኦነግን በማዳከሙና ኣባላቱን በመከፋፈሉ ተግባር ላለፉት ኣስርት ኣመታት ትልቁን ሚና ሲጫወቱ የኖሩት እነዚሁ ወገኖች መሆናቸውን እንደገና ለማስገንዘብ እንገደዳለን። ለዚህ ደግሞ ከበቂ በላይ የሆኑ የቪድዮ፣ የድምጽና የጽሁፍ ማስረጃዎች ያሉ ሲሆን ኣስፈላጊና ኣመቺ በሆነ ጊዜ በስፋት ለህዝብ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

የስብስቡ ኣመራሮች ባገኟቸው ኣንዳንድ የሚድያ ኣጋጣሚዎች ላይ እንደመሰከሩት ሁሉ የውይይቱ ኣብይ ኣላማ ኦነግ የሚመራበትን የትግል ስልትና ስትራቴጂ መቀየር ነው። ከጥቂት ቀናት በፊት የወጣው የዚሁ ስብስብ መግለጫም ይህንኑን ያረጋግጣል። ይሁን እንጂ የኦነግን ድርጅታዊ ኣሰራር በቅርበት የሚገነዘብ ማንኛውም ወገን እንደሚረዳው የድርጅቱን የትግል ስልትና ስትራቴጂ የመቀየር መብት የተሰጠው ጠቅላላ ጉባኤው (Kora Sabaa) ብቻ ነው። ኦነግ በጠቅላላ ጉባኤው ላይ ባጸደቃቸው የትግል ስልቶችና ስትራቴጂዎች ይመራል። የትግል ስልቱንና ስትራቴጂውን ማሻሻል ሲያሻው ደግሞ ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቶ መሰረታዊና ኣስፈላጊ ያላቸውን ግምገማዎች ኣካሄዶ የጉባኤውን ብዙሃን ድምፅ ያገኘ ውሳኔ ያጸድቃል። ያ እስካልሆነ ድረስ ማንኛውም ቡድን ባሻው ጊዜ ብድግ ብሎ የኦነግን የትግል ስልትና ስትራቴጂ የመቀየር መብትም ሞራልም የለውም።

ህዝባችንም ይህንን ሃቅ ይበልጥ በመገንዘብ ለመሪ ድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራም ዘብ መቆምና ከድርጅቱ ኦነግ በየጊዜው የሚቀርቡለትን የትግል መመሪያዎች ገቢራዊ ለማድረግ ከማንኛውም ጊዜ በላቀ መልኩ በንቃት እንዲንቀሳቀስ ጥሪ እናቀርባለን። የኦሮሞ ህዝብ በማናቸውም ጸረ-ኦነግ ፕሮፓጋንዳዎች ሳይታለል ውድ መስዋእትነቶችን ሲከፍልበት እስከ ዛሬ የዘለቀውን ትግሉን ከግቡ ለማድረስ ይበልጥ ከመሪ ድርጅቱ ጎን ተሰልፎ ድርሻውን በእጥፍ ድርብ እንዲያሳድግ ጥሪያችንን እናድሳለን። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኣሁን ባለው ኣጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ከዋነኛው የትግል ጎዳና ሊያስወጡን ለሚፈልጉ ኣላስፈላጊ ግፊቶች ሳንበገር በሚፈጠሩ ኣጋጣሚዎች ሁሉ ለመጠቀም በትጋት መንቀሳቀስ እንዳለብን መልእክት ማስተላለፍ እንወዳለን።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር

ነሓሴ 01, 2012